# አዲስ ሆኖ ከመቅለል አሮጌ ሆኖ መሰቀል!

አሁን ምንያደርጓል የጊዜን ደሳሳ፣
አሮጌ ቤት አይደል በባላ አይነሳ።

“ክፉንም ደጉንም ሰምተን መጣን“ አለ አሉ ጅብ። እነዴት ቢሉት፣ ደጉ አህያ ጠፋች ሲሉ መስማታችን ሲሆን፣ ክፉው ደግሞ ሰዉ ሁሉ ጦር ያለህ ጦርህን፣ ገጀራ አለህ ገጀራህን ይዘህ ውጣ፣ እተባባሉ ሲጠራሩ መስማታችን ነው፣ አለ ይባላል። እኛም እለት እለት የምንሰማውና የምናየው ነገር ሁሉ እንዲሁ ውል እያጣብን ተቸግረናል።

በውጭም ይሁን በሀገር ውስጥ ያለው የፖለቲካ አካሄድ፣ እንደ አዳኝ ለመብላት ሲባል መግደል በሚባል መርህ የተለወሰ ነው። አምባገነኖች ደግሞ ጥማቸውን ለማርካት ሲሉ፣ አዲስ ከተወለደ ህጻን ጉሮሮ ፈልቅቀው፣ ከወላድ እናት የጡት ወተት የሚዘርፉ ዓይነት ናቸው። ስለሆነም ለዓላማቸው የጨከኑ። በደማቸው ሳይቀር አነሱንና የነሱ የሆኑትን ብቻ የሚመግቡ፣ ውስጣቸው በድንጋጤ ድባብ የተሞላና ከፍርሃታቸው የተነሳ በጨለማ የሚተኩሱ፣ የህዝብ ፍቅር፣ የሀገር አንድነትና ሰላም እንደ ቀትር የአቀበት ጉዞ የሚተናነቃቸው፣ ለመገንባት ሳይሆን ለጥፋት የተሳሉ፣ በአይምሮ ዋሻ ውስጥ የጥፋት ባህር ሠርተው የሚዋኙ፣ ውስጣቸው በእብሪት የታጨቀና የሰው ህይወት ቀሳፊ አውሬዎች ናቸው ማለት ይቻላል። ታሪክም ዳስሶ ያሳየን፣ እኛም በዚች ትንሽ ዕድሜ የታዘብነው እውነታ ቢኖር ይህንኑ ነው።

ምንም እንኳ ተፈጥሮ የተዋበ የነጻነትና የፍትህ ሞገስ ለሁላችንም እኩል አጎናጽፋን ሳለ፣ በጉሳ ሌጦ የተለበዱት የዘመኑ ዘረኛ አምባገነኖች ደግሞ፣ ጠባብ የጎሰኝነትን ካባ ሊደርቡብን ይታገላሉ። የሰላም ሀብታችንንም እየዘረፉ ነፍስና ስጋችንን እያጎሳቁሉ ስለመኖራቸው በገሀድ የሚታወቅ ጉዳይ ነው።

የታሪክ መዘክር እንደሚያስረዳው፣ ባቢሎንን ያፈረሰው፣ የኢየሩሳሌምን መሠረት ያናወጠው፣ የሮማና ጀርመንን ወ.ዘ.ተ ታሪካዊ ገጽታቸውን ያጎደፈው፣ እነሆ ስልጣንን አለአግባብ መጠቀም ነው።  ወያኔ ደግሞ ገና ሲፈጠር ጀምሮ ሲያራምደው በነበረው አቋምና የፖለቲካ አካሄድ (እስትራቴጂ) ሳቢያ ስህተት ውስጥ የገባ ድርጅት ነው። ይኸው ስህተቱ  ወደጥፋት ተሸጋገሮ እነሆ በአሁኑ ወቅት ሀገርንና ህዝብን እያወደመ ስለመገኘቱ፣ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም በገሃድ እየታየ ያለ ሃቅ ነው።

ይኸው የስልጣን አባዜ በሀገራችን ላይ እንደ ምርጊት ከወደቀባት ጊዜ ጀምሮ ገጽታውን እየቀያየረ ፍዳዋን ያሳያታል። ይህን አስከፊ ሁኔታ ለመለወጥ በሚደረገው እልህ አስጨራሽና ረዝም መራራ ትግል ውስጥ፣ ቀንበሩን እንደሚያፈቅር በሬ በእርሻው (በትግሉ) ተጠምዶ ሳለ የጫካውን (የከተማውን) አጋዘን አውደልዳይ (ባንዳ) ቢለው ሐጢአተኛ ሊያሰኘው የሚገባ አይመስለኝም።

መቸም ፈጣሪ ሁሉም ነገር አምሳያ አያሳጣውምና እነሆ እብሪተኞች ያልፈጠረባቸውን በጎ ገጽታ እየሳሉ ህዝብን ሊያውገረግሩን የሚሞክሩ ጋሻጃግሬዎች አሏቸው። ይህን ክስተት ደግሞ ቀድሞ ከታየውም ይሁን አሁን ካለው የታሪክ አጋጣሚ በጉልህ ያየነው ጉዳይ ነው። ለዚህ መሰሪ ለሆነና ሃላፊነት ለጎደለው ተግባር ሥራቸው ዋቢ የሚሆነን፣ በአሁኑ ጊዜ ይኸው ጥምር ሴራቸው (የአምባገነኖችና ባንዶቻቸው)፣ ጉልበት አውጥቶ ባህር እስከመሻገር የደረሰና በውስጥም በውጭም የጥፋት ተልእኮአቸውን በሚገባ እንዲወጡ ያስቻላቸው ሁኔታ መታየቱ ነው።

ከዚህም የተነሳ፣ ዛሬም ቢሆን በተኩላዎች መሀል እንደተገኘ ጠቦት፣ መሀል ምንገድ ላይ ቆመን ፍርሀት ይሰማናል።  ስለሀገር ብለን በጨካኞች በታፈንና በታረድን፣ በተሰቃየንና በተሰደድን፣ ሁሉን ችለን በአምላክ ቸርነት ለዚህ መብቃታችን፣ የሚያስመሰግን ሆኖ ሳለ፣ እውነቱን ለመቀበል የሚተናነቃቸው በርካቶች ናቸው። ያም ቢሆን ያበረታን እንደሁ እንጅ መንፈሳችንን ሊያዝለው የሚችል ጉዳይ ይደለም።

ይሁን እንጂ፣ ለአለፉት በርካታ አስርተ-ዓመታት፣ ኢትዮድያ ያጣችው ነገር ቢኖር ሐብት ሳይሆን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው። ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ደግሞ ዲሞክርሲያዊ ባህሪ ባለው መንግስት የሚገነባ ነው። ያም ማለት ቢሆን፣ በህዝብ የተመረጠ የህዝብ የሆነ መንግስት ማለት ነው። ቁምነገሩ ስልጣን የህዝብ፣ ከህዝብ ለህዝብ ሲሆን ማለት ነው። በዚህ ረገድ ከደርግ ውድቀት በሁዋላ በሀገራችን ይሰፍናል ብለን በተስፋ ስንጠባበቅ የነበረው የፍትህና የሰብዓዊ መብት መከበር ጉዳይ እነደ ጉም በኖ ከፊታችን ሲጠፋ አስተውለናል፡፡

አሁን ምን ያደርጓል፣ የሆድን ህመም፣
ማጭድ አይገባበት፣ በእጅ አይታረም።.....ነው ጉዳዩ፣

አሁን በአለው የፖለቲካ ቸነፈር ሳቢያ፣ እንደ ደረቀ ጭራሮ ማንም መንገደኛ እየማገደን እንዲያልፍ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ይህንን አፍራሽ ተልእኮ መቀልበስና የትግሉን እርምጃ መልክ ማስያዝ እጅግ አስፈላጊና ወቅታዊው ተግባር ነው።

ከመቼውም ጊዜ ይልቅ፣ አመቺ የትግል ወቅት እየተፈጠረ ስለመሆኑ ያሉት ተጨባጭና ነባራዊ ሁኔታዎች በግልጽ ይጠቁማሉ። ይህንን የታሪክ አጋጣሚ በማየት፣ ኢትዮጵያዊ ጠረን ያላቸው የአንድነት ሃይሎች ሁሉ በአንድ መምከርና የሃይል አሰላለፋቸውን ረድፍ ማሰያዝ ያስፈልጋቸዋል።

በዚህ ረገድ ለሁለገብ ትግል ጥሪ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ወንዝ ተሻግሮ የዘለቀ አወንታዊ እርምጃ መውሰድና የተቀናጀ ፖለቲካዊ አመራር እንዲፈጠር ማድረግ የግድ ይላል። እሱም ቢሆን ፈቃደኝነትን፣ ቆራጥነትን፣ ዝግጁነትን ፣ በዲሞክራሲያዊ አሠራር የዓላማና የትግል ስልት ማጣጣም እና በሀበሻ ወግና ቤተሰባዊ መከባበር ለውጤታማነቱ ተግቶ መስራት ያስፈልጋል። ምን ጊዜም ቢሆን የጠላትም ሆነ የወዳጅ ትንሽ የለውም። ወዳጅ በዘመን ሁሉ ሊወድ ይችል ይሆናል።  ነገር ግን ጠላትን መናቅ የውድቀትን የመጀመሪያውን ምእራፍ ማስናገድ ነው የሚሆነው።

ምን ያደርጋል ዱላ ጅና ቢያበዙበት፣
እንደሰባራ ቅል ካልተረተሩበት።.......ሲባል ነው እንጅ፣

ደግሞም ሰይጣናዊ አስተሳሰቦች እንጅ፣ ሰይጣናዊ ስጦታዎች በዓለም ላይ የሉም። የሰው ልጅ የበጎም የክፉም ተግባር ምንጭ ነው። ሰው በሃሳቡ ረቂቅ እንደሆነ ሁሉ፣ በሥራውም ውስብስብ ፍጥረት ነው። ለዚህም ይመስለኛል፣ ፈላስፋዎቹ “ ሰው ተነቦ የማያልቅ መጽሐፍ ነው “ የሚሉት። የዓለም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ምስቅልቅሉ እየወጣ ያለው ከዚሁ ውስብስ ባህሪው የተነሳ እንደሆነ እገምታለሁ። ሀገራችንም አንዷ የዚሁ ክስተት ገፈት ቀማሽ መሆኗ አያስደንቅም።

በሃሳብና በስልት ልንለያይ እንችላለን። ቁምነገሩ ግን ልዩነታችንን በአወንታ ተቀብለን ለእድገታችን ሊጠቅም የሚችለውን ንጥረ-ነገር ፈልቅቀን በማውጣት ጥቅም ላይ ማዋል የመቻሉ ጉዳይ ሲሆን፣ ሁላችንንም አጋምዶ ወደፊት ሊያራምደን የሚችለው አቢይ መልህቅ ይኸው ጭብጥ ነው።

ነገርና ገመድ ሲከር አይወድለት፣
እስኪ ሰላ በሉ፣ መላ እንዲገኝለት።

በአሁኑ ጊዜ በገሀድ እንደሚታየው፣ “ ሀበሻ አብሮ መብላት እንጅ፣ አብሮ መስራት አይሆንለትም “ የሚለው አባባልም ህያው ሆኖ እንዲዘልቅ የብዙዎቻችን ድጋፍ የተቸረው ይመስለኛል። የአብሮነትን ገመዳችን ለመቁረጥ እለት ተእለት ለሚሳለው የጎጠኝነት ጎራዴ ሃይል ሰጭ ስለመሆኑ ብዙዎቻችን ልብ ያልነው ጉዳይ አይመስለኝም። ደግሞስ በአካልም ይሁን በመዋቅር፣ አለያም በሀብትና በዝና ገዝፈን፣ ነገር ግን በመንፈስ፣ በሞራልና ፍልስፍና ረገድ ኮስሰን ብንታይ በእርግጥ ሊታዘንልን የሚገባ ምስኪኖች አይደለንምን? በዛሬውስ የጽልመት ገጽታ ውስት ቆመን፣ የነገን የነፃነት አግማስ በጎህ ንቃቃት ውስጥ አሻግረን መቃኘት አለመቻላችን፣ እርምጃችንን ምን ያህል ሰንካላ እያደረገው እንደሆነ ስንቶቻችን አስተውለን እናውቅ ይሆን?

አንዳንድ ጊዜ ካለማስተዋል፣ ከትግል ባህሪ ውስብስብነትና ከውጣ ውረዱ ዝለት የተነሳ፣ በጽናት ቆመን ጥቂት ተጨማሪ ማይል መጓዝ አቅቶን፣ የድልን ፋርቱና በክንዳችን ላይ  እንዲያሸልብ ልናደርግ እንችላል። ስለሆነም ከእውነታው ጋር የማይጣረስ የማትጊያ መረዋ በእያንዳንዳችን ህሊና ውስጥ ተሰቅሎ አካሄዳችንን ሊያሰምረው ይገባል። ምክንያቱም ሁልጊዜ ድል በለስ የቀናውን ማክበር ልማዷ በመሆኑ፣ እውነተኛ ወዳጇኝ የማታውቅ እውር አፍቃሪ ነች። አንገቱን ለሰይፍ የሰጠላትን እውነተኛ አፍቃሪዋን ጥቂት ቆማ ለመጠበቅ ትዕግስት ከቶ የላትም። “ እናቴን ያገባ ሁሉም አባቴነው “ ባይ ስለሆነች የሁል ጊዜ ዝግጁነት ያስፈልጋታል፡፡

ለራሳችን መተኛት ስንፈለግ ያለፍላጎታቸው ልጆቻችንን እሹሩሩ ብለን እንደምናስተኛ ሁሉ፣ ከትግሉ አውድ እፎይታ ባሻን ወቅት፣ የትግሉን ሙቀት እያባበልን ወደሰመመን እየወሰድነው ያለን እጅግ በርካቶች ነን። ይህ ደግሞ በራሱ ድንዛዜ ፈጥሮ እንደ ወረርሽኝ ከአንዱ ወደሌላው እየተዛመተ፣ በርካታ ፋኖዎችን ከትግሉ አውድ እያስፈነጠረ ያለ ሲሆን፣ ከዚህም ባሻገር የፖለቲካ ዛር ሆኖባቸው በየቤቱ መሸገው በህሊናቸው፣ እንዲያም

ሲል በድህረገፅ የውይይት መድረኮች (በሳይቨሩ ሜዳ) ሲታኮሱ የሚያድሩ የመንፈስ አርበኞች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደለም።

አርበኝነትም ቢሆን እድል በጠላት እጅ ምርኮ በሆነችበት ወቀት፣ ፈቷን ወደራስ የምታዞርበትን አስገዳጅ ሁኔታ መፍጠር መቻል ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ የተለየ ሥራ መስራትን አይጠይቅም። ነገርግን በዓላማ ፀንቶ፣ ከሌላው በተሻለ ሞራልና ወኔ ረዘም ላለ ጊዜ እየተፋለሙ መቆየት መቻል ነው። “ ሶቅራጥስ ስለእውነት፣ ክርስቶስ ደግሞ ስለሰው ልጅ ደህንነት “ መሞታቸውን ልብ ይሏል።

“ ብረት በግለቱ ” ነውና፣ የበረደ ነገር እንኳን ለፍትህና ለዓርነት በሚደረግ የመስዋእትነት ተጋድሎ፣ የመንደር ፍቅር እንኳ ቢሆን አያሰልጥም። ሁሉም ነገር የሚያምረው በወጉና በፈርጁ ሲሆን ነው።

ከወንዝ ወዲያ ማዶ አውድማ ጥለሽ፡
እኔን አረብራቢ አርገሽኝ ከረምሽ።....ሊያሰኝ ይገባል፣

እንደ እኛ የሚንገላታ ትውልድ ለማፍራት ነገን ተበድረን የአመጽ እረሾ አቡክተን ልናቆየው አይገባም። እኛ ያቦካነውን እኛው ጋግረን የማለፍ ሃላፊነትን አለብን። ምክንያቱም የነገን ምላሽ የምናሰምረው ዛሬ በተግባር በምናስመዘግበው አወንታዊ እርምጃችን የልኬት መጠን ነው።

የዓይናችው ቅድ የእኛ ለሚመስሉት ሁሉ ከእንባ ይጠበቁ ዘንድ፣ ተግቶ መስራት ይጠበቅብናል። የታደሉት አባቶቻቸው፣ በነጻነት ላይ የጥሪት ካባ እንደሚደርቡላቸው፣ እንዲሁ የእኛም አባቶቻችን ከስልጣኔ ባሻገር፣ የነፃነት አርማችንን ከፍ አድርገው  በሰንደቅ እያውለበለቡ ለዘመናት በመኖራቸው፣ አንገታችንን ለአንዴዬ እንኳ አላስደፉንም። ይልቁንም በአንፃሩ ፈርሐ እግዚአብሄርን፣ ኢትዮድያዊነት ኩራትን፣ ከደለበ የተፈጥሮ ሐብትና ከሚያስደምም የታሪክ ድጓ ጋር በአደራ አስረክበውን አልፈዋል። እንዲያ ባይሆንማ ኖሮ “ መወለድ ቋንቋ ነው “ ብለን፣ ሌሎች እንዳደረጉት የተውሶ ማንነት ፍለጋ ብዙ በማሰንን ነበር።

ያለፈው ትውልድ በአብዮት ስም ጨካኞች በለኮሱት የሰደድ እሳት በመበላቱ ሳቢያ፣ በትውልድ መሃል ክፍተት በመፈጠሩ ከፍተኛ ብሔራዊ ጉዳት ነው በሀገርም በመሪው የፖለቲካ ድርጅት ላይ ያስከተለው። አሁን ያለው ተተኪው ትውልድ ደግሞ ከደርግ የመከራ ዘመን አብራክ የወጣ በመሆኑ፣ የዛን ትውልድ ወኔና የተጋድሎ ታሪክ በውል አያውቀውም። ለማወቅም ፍላጎት ያላቸው ውሱን ናቸው። ሀገሪቱ የባእዳን፣ የባህልና የሐብት ወረራ በስፋት በሚያተራምሳት፣ እና ቴክኒዮሎጅ ባማለለው በዚህ “ የፋፋ “ ትውልድ መሀል ቆመን የምንሰብከው የኢትዮድያዊነት ገድልና ፖለቲካ፣ ምን ቅርፅና ይዘት፣ ምን መጠንና ስልት ሊኖረው እንደሚገባ አስቀድሞ ሊጤንበት የሚገባ ወቅታዊ አጀንዳ ነው። የሰው ልጅ ጉዳቱም ጥቅሙም ልቡ የሸፈተ ዕለት ነው።

“ መካንና ጸሐይ እየሞቀ ያደኸያል፡ ወላድና ዝናብ እየቀዘቀዘ ያከብራል “ እንዲሉ፣ አብዮት ረዥም እጅ አለው ሞገዱ ሲነሳ ሁሉንም መዳሰስ ይችላል። ምንም እንኳን ስነ-ምግባራችን እንደመልካችን ቢለያይም፣ በድርጅትም ይሁን በግል እጃችሁ ከምን አይነት መጠየቃችን አይቀሬ ነው።  በሀረገራችን እንኳን ፖለቲካው ለቅሶም የራሱ ለዛ አለው አይደል፡-

“ ማልዶ ለመጣ ሰው ማልጄ እሄዳለሁ።.....
አርፍዶም ለመጣ አርፍጄ እሄዳለሁ፡፡
አዳራሹ ሰፊ ለምን አኮርፋለሁ “

የጓዶቻችን መሰዋዕትነት ለእኛ የጽናታችን መሰረት ነው። ስለሆነም ለዓላማ ቆርጦ መነሳትና ያለመታከት አስቸጋሪውን የትግል ዳገት ተቋቁሞ  ወደፊት በትግል ጽናት መራመድ መቻል የአሸናፊነት ጀልባ መቅዘፍ ማለት ነው፡፡ በታገልን ቁጥር፣ ወደ ድልና ሃያልነት ልዕልና እየተቃረብን እንደምንሄድ ማወቅ አለብን። ምንጊዜም ቢሆን “ የሰው ልጅ ብርቱ አላማ ሠራዊት ካሰለፈ የጠላት ሃይል ብልጫ አለው “ የሚባለውን ሀቅ፣ ብዙ ሩቅ ሳይኬድ  የኢ.ሕ.አ.ፓ የትግል ተመክሮ ያረጋግጥልናል።

እናንት የማለዳ ዛፎች ህያው ሆናችሁ ስትንቀሳቀሱ በዜጎችና ሀገር ወዳድ ወገኖች ልብ ውስጥ የተሰፋ ምናብ ሆናችሁ። ራእያችሁ ትውልዱን ሲያንቀሳቀሳ የኖረውን ያህል፣ ዛሬም ቢሆን የታሪክ መዘውር ሆናችሁ የትግሉ ወኔ እንዳይመክን ታደርጉ ዘንድ ታላቅ ሃላፊነት እንዳለባችሁ እናውቃለን። በአንፃሩ ከቀሪው ትግልና ከሚጠይቀው መስዋዕትነት አኳያ ሲመዘን፣ ማልዶ መነሳት ብቻውን በቂ እንዳይደለ፣ ማልዶ መተኛትም ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እጅግ እያመዘነ እንዳለ መጠቆም እወዳለሁ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ትጋት ቀዳሚው የውጤት መለኪያችን እንዲሆን ምኞቴ ነው። ታላቁ መጽሐፍ ስለህይወት ዝለት ሲመክር፣ “ መኝታን የሚወድ

የተቀዳደደ ልብስ ይለብሳል “ ይላል። ይህ ቁምነገር በሁሉም የእንቅስቃሴ ዘርፍ እውነትነት አለውና በብርቱ ሊታሰብበት ይገባል።

ፈረሴን ጫኑልኝ፣ ያንን ዳማ ቦራ፡
መከራም ደስታ ነው፣ ከኢትዮጵያ ጋራ።.....ተብሎ የለ፣

እኛ ከሁለት ታላላቅ ዛፎች የተገኘን ዘሮች ነን። ከኢትዮጵያዊነትና ኢ.ሕ.አ.ፓነት። የፋኖነታችን ሐረግ የሚመዘዘው ከእነዚህ ሁለቱ አድባር አምዶቻችን ነው። በአንድ ድርጅት ጥላ ስር መሰባሰባችንም ለዝክረ ሰንበቴ አለያም እንደሌሎች የፖለቲካ መጋኛ ተጠናውቶን አይደለም። የህልውናችንና የመብታችን መሠረት ከድርጅታችን ማጀት እንደሚቀዳ ስለምናምን ነው። የድረጅት የፖለቲካ ጉዞና ስኬት ደግሞ አምነው በሚከተሉት ሰዎች ብስለትና ጥንካሬ ይወሰናል። የተሻለ የፖለቲካ አካሄድ የሚኖረው በቅድሚያ እያንዳንዳችን የተሻለ ማድረግ ስንችል ብቻ ነው። የእኛም ሆነ የድርጅታችን ማንነት በአጋጣሚ የተፈጠረ ነገር አይደለም። ነገር ግን አጋጣሚዎች ማንነታችንን ገልጠው ሊያሳዩ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ብዙዎቻችን የምንመራው በተሞላነው ፕሮግራም ነው። ለሀገራችንና ለህዝባችን የምንናፍቀውን ፍትህና ነጻነት እውን ማድረግ የምንሻ ከሆነ ደግሞ ዛሬም ቢሆን መሸ እንጅ አልነጋብንም። ተቀያሪዋ ኳስ በእጃችን እንደምትገኝ የዘነጋን ጥቂቶች አይደለንም። ጨዋታው በዙር ሳይሆን የጥሎ ማለፍ ነው። ግማሽ ልምምድ አድርጎ ሙሉ ጨዋታ መጫወት አይቻልም። “ የሞኝ ዘፈን ሁልጊዜ አበባዬ “ እንዳይሆንብን ተገቢው ጥንቃቄ ሊኖረን ይገባል። መውደቅን እየፈሩ አለመጫወት ትግልን ማሽመድመድ ነው። ሽንፈት አማራጭ ባይሆንም አስተማማኝ ስኬት ከውድቀት ጀርባ ሰለመኖሩ ቅንጣት ያህል ልንጠራጠር ከቶ አይገባንም።

ነገር በምሳሌ ነውና፣“ በአንድ ወቅት በአንድ ስፍራ አሳማና ዶሮ ወዳጅ ሆነው አብረው ባንድ ማድ እየቆረሱ ይኖሩ ነበር። አሳማ በባህሪው ሆደሰፊ በመሆኑ፣ ዶሮ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በሁኔታው መማረር ትጀምራለች። በዚህ ሁኔታ እየኖሩ እንዳሉ፣ ከእለታት አንድ ቀን የጋራቸው የሆነ የሚወዱትና የሚያከብሩት እንግዳ ሊጎበኛቸው ወደ እነሱ ሊመጣ ሆነ። እነሱም በመስተንግዶው ዙሪያ ማሰብና መመካከር ይጀምራሉ። ብዙ ካወጡና ካወረዱ በሁዋላ ዶሮ አንድ ሀሳብ ይመጣላትና ለአሳማ እንዲህ ትለዋለች። አንግዲህ እንግዳችን ትልቅ እንግዳ ነው ደስ የሚለውን ምግብ አዘጋጅተን ልንጋብዘው ይገባናል። አሳማም ሀሳቧን ከተቀበለ በሁዋላ ታዲያ ምን ይሻላል? ምንስ ልናዘጋጅ እንችላለን፣ የሚዎደውስ ምግብ ምን ሊሆን ይችላል? በማለት ደግሞ ይጠይቃታል። እሷም መለስ አርጋ ሞረቶዴላ በእንቁላል እንደሚዎድ ሰምቻለሁ ትለዋለች። አሳማ ጥቂት ካሰበ በሁዋላ አዬ ዶሮ! ይህማ ለአንች መዝናናት ነው፣ ለኔ ግን መስዋእትነት! ነው “ አላት ይባላል። የኢትዮጵያና የኢ.ሕ.አ.ፓ ጉዳይ ለሌሎች ሌላ ሊሆን ይችላል። ለእኛና አኛን መሰሎች ግን፣ የደም ዋጋ፣ የህይወት ምንዳ፣ የማንነት ስንክሳር፣ የአባቶች አደራ፣ የፈጣሪ ትሩፋት፣ የመኖርና ያለመኖር ማተብ ነው።

እንደ አይን እንደ ጆሮ፣ እንደ እግር እንደ እጅ፡
ወዳጅ አብሮ ሆኖ፣ ሲባክን ነው እንጅ።......የሚባለውም ለዚህ ነው፣

ድል የጥረትና የአጋጣሚ ውጤት መሆኑ ይታወቃል። በትግሉ ተሳትፎ ዙሪያ የላቀ ድርሻ እንዲኖረን ከተፈለገ፣ የውስጥ ፍላጎቶቻችንንም ይሁን ሌሎች ጎታች አመላካከቶችንና ፍላጎቶችን ከላያችን ላይ አራግፈን፣ በፍጥነት በአዲስ ራዕይ ወደፊት መራመድ ይጠበቅብናል። አቅምን መገንባትና ሁኔታዎች በሚፈቀዱት መጠን የሚቻለውን ሁሉ ከማድረግ አለማሰለስ ሌላው ሊተኮርበት የሚገባ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ሌላው ቢቀር እንኳ “ በውቤ ጊዜ የደነቆረ፣ በውቤ አምላክ ሲል ይኖራል “ ከመባል ያድነናል።

ሀገርና ድርጅት ደግሞ መሪዎች በሚሰጡት ማዕካለዊ አመራር ብቻ አይገነቡም። የሁሉም ዜጎች በጎ ምላሽና ከዛም ያለፈ አወንታዊ ርብርብ ያስፈልጋቸዋል። እንደዜጋም ይሁን እንደ ፖለቲከኞች ስናስብ ሲኖረን የሚገባው አቋም፣ እያንዳንዳችን ለሁላችን፣ ሁላችንም ለእያንዳንዳችን ህልው፣ እድገትንና ውጤታማነት ተግቶ የመስራት፣ ሀገራዊ፣ ድርጅታዊ ግዴታና ሀላፊነቱ እንደሆነ ማረጋገጥ መቻል ነው። ነጻነት፣ ፍትህና እኩልነት የሚያስገኘው ቀዳሚው አሴትም ይኸው ነው።
ስለሆነም የአንደኛው ህይወት ማጋደል ሌላኛውን ሊያሳስበው ይገባል። ሀገር በጥቂቶች አትገነባም፡ በአንድ ጀምበርም ለምታም ፈርሳም ከቶ አታውቅም። ለዚህም ነው የሀገር ጉዳይ ለእኛ ለኢ.ሕ.አ.ፓ ደጋፊዎች የእድሜ ልክ የቤት ሥራ የሚሆንብን። ሁልጊዜ ስለሀገር ስናወራ የስጋታችንም ይሁን የተስፋችን ምንጭ ይኸው ኢትዮጵያውነታችንን የማስከበሩ ጉዳይ ቀዳሚው አዠንዳችን በመሆኑ ነው።

ይሁን እንጂ፣ የተማከለ የህሊና ዳኝነት ከሌለው ማንኛውም የፖለቲካም ይሁን የታሪክ ጉዞ ውስብስብና የመከራ ቋት ነው። የአምባገነኖች ትልቁ ችግራቸው የህሊና ሚዛናቸው የተዛባ መሆኑ ነው። ስለሆነም እናንት

የፖለቲካ ሰዎች! በስጋቸው ታማኝ ሆነው በመንፈስ ሌባ ለሆኑ ሰዎች ምን ፍርድ ትሰጣላችሁ? በስጋቸው ለሚያርዱ ነገር ግን በመንፈሳቸው ለታረዱስ ምን ብይን ይኖራችሁ ይሆን? የእኛ የትግል ታሪክ እነዚህን ትንግርታዊ ክስተቶች ያስተናገደ መድረክ እንደመሆኑ መጠን፣ ለሚዛናዊው የህሊና ወቀሳና ፍርድ መዘጋጀትና በማስከተልም አግባብ ያለው አወንታዊ እርምጃ መወሰድ ያለበት ጊዜ አሁን እንደሆነ ብጠቁም፣ ከተጨባጭ ስጋት የመነጨ ጉዳይ እንጅ በባዶ ሜዳ ወልይ መሆን አምሮኝ አይደለም። “ ሻይቃጠል በቅጠል “ እንዲሉ ያስተውሏል።

ማንኛችንም ብንሆን ነገ ሰለመምጣቱ እርግጠኞች አይደለንም። ያለፈንም ይሁን የዛሬን ቁጢት ዘሬ ላይ ቋጭተን፣ በሌላ ምዕራፍ ነገን በተስፋ ልንጠብቀው ይገባል። ማንያውቃል ጎበዝ! ማምሻም እድሜ ነውና ነገ ግዳይ እንጥል ይሆናል። ያም ሆነ ይህ በሀገር ቤት ምክሩ፣ “ የንጉስ ዙፋን ሲናወጥ ወንበርክን አትልቀቅ “አይደል? ደግሞስ በአሮጌ ማድጋ የተጠመቀ ወይነጠጅ ቃናውን እንደማይለውጥ አይደል እናቶች የነገሩን። ስለዚህም አዲስ ሆኖ ከመቅለል፣ አሮጌ ሆኖ መሰቀል ሳይበጀን ይቀር ብላችሁ ነው? ለዛሬው ሃሳቤን እዚህ ላይ ልግታና በምስጋና ልሰናበታችሁ! በሉ ለቀጣዩ አማን ያገኛችሁ።

አሙን አሙን አሉ ተዋቸው ይሙን፣
ቢፈሩን አይደል ወይ ቢጠረጥሩን።

ቁጠማው ይንዝንዝ፣ እጣኑም ቡል ይበል
ቡናውም ይፈላ፣ ሀድራውም ሞቅ ይበል
ፋኖው ይሰባሰብ፣ ሆታው ደመቅ ይበል
የእኛ ቤት ከራማ፣ እንግዳ ይወዳል

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ !!!**

**እናቸንፋለን !**

አክሊሉ ሃይሉ
Ahailu99@gmail.com
(ፍርንክፈርት - ኖቬንበር - 2011)